16ኛ ዓመት ቁጥር 29
16th Year No. 29

ባሕር ዳር ህዳር 12 ቀን 2004 ዓ.ም
Bahir Dar November 22, 2011

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 2.60
Unit price 2.60

## ማውጫ

**አዋጅ ቁጥር 191 /2003ዓ.ም**

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተርን ኦቨር ታክስን ለማስከፈል የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ**

## Contents

**Proclamation No.191 /2011**

**A Proclamation Issued to Amend the Amhara National Regional State Turn over Tax proclamation**

## አዋጅ ቁጥር 191 /2003ዓ.ም

## በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተርን ኦቨር ታክስን ለማስከፈል የወጣው አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሥራ ላይ ያለውን የተርን ኦቨር ታክስ ማስከፈያ አዋጅ ቁጥር 83/1995 ዓ/ም ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጇል።

## Proclamation No.191 /2011

## The Amhara National Regional State Turn Over Tax Proclamation Amendment Proclamation

Whereas, it has become necessary to amend the Turn Over Tax Proclamation No. 83/2003, which is in effect in the Amhara National Regional State ;

Now, therefore; the Council of the Amhara National Region, in accordance with the Powers vested with it under Sub-Article 3/1 of Article 49 of the Revised Constitution of the Region, hereby proclaims as follows:

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ ''በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተርን ኦቨር ታክስ ማስከፈያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 191 /2003 ዓ/ም » ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ማሻሻያ

በሥራ ላይ ያለው የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 83/1995 ዓ/ም እንደሚከተለው ተሻሽሏል፣

ሀ/ የአዋጁ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ /1/ ፊደል ተራ ቁጥር /ሀ/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ ቁጥር /ሀ/ ተተክቷል፦

"ሀ. የእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ ወይም እርሱ ለሚወክለው የፋይናንስ ተቋም ወይም በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴ የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቂያ በማቅረብ መክፈል የሚገባውን ታክስ ወዲያውኑ የመክፈል፣"

ለ/ ከአዋጁ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ /2/ ቀጥሎ የሚከተሉት አዳዲስ ንዑሳን አንቀጾች 3፣ 4፣ እና 5 ተጨምረዋል፡፡

3. በታክስ ከፋዩ የንግድ ስራ ቦታ በመገኘት ምርመራ ለማድረግ ስልጣን የተሰጣቸው የባለስልጣኑ ሠራተኞች ማናቸውንም ህገ ወጥ ደረሰኝ ወይም የሂሳብ ሰነድ ወይም የሂሳብ መዝገብ ካገኙ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሳያስፈልግ ህገ ወጥ የሆነውን ደረሰኝ ወይም ሰነድ መያዝ ይችላሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ የተያዘው ሰነድ በማስረጃነት በፍርድ ቤት ዘንድ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

4. ህገወጥ ደረሰኞችን ወይም ሰነዶችን ለመስጠት ፈቃደኛ ባልሆነ ግብር ከፋይ ላይ የፖሊስ ኃይል ወይም ሌላ የህግ አስከባሪ በመጠቀም ህገወጥ ደረሰኙን መያዝ ይችላል ፡፡

5. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 አፈጻጸም በባለስልጣኑ ሠራተኞች ትብብር የተጠየቀ ማናቸውም የፖሊስ መኮንን ወይም የህግ አስከባሪ አካል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "The Amhara National Regional State Turn over Tax Proclamation Amendment Proclamation No. 191 /2011."

## 2. Amendment

The turn over Tax Proclamation No.83/ 2003 is hereby amended as follows:

A. Paragraph (a) of sub article 1 of article 10 of the proclamation is repealed and replaced by the following new paragraph (a) :

a. "File a turn over return and simultaneously pay to the tax authority or to a financial institution delegated by the tax Authority or through electronic filing and payment system with in one month after the end of every accounting period."

B. The following new sub- articles 3, 4 and 5 are inserted next to sub- article 2 of article 12 of the proclamation:

3. Duly accredited inspectors of employees of the Authority, if they get illegal receipt or records of books of accounts at the place of business of the tax payer, the can seize the same without a court warrant. Such a document has admissibility before a court of law.

4. It may be possible to seize the illegal documents with the help of police force or other law enforcer, if the tax payer fails to hand over the illegal receipts of records.

5. Any police officer or law enforcement body is duty bound to cooperate with employees of the Authority for the implementation of sub- article 3 of this article.

ሐ/ የአዋጁ አንቀጽ 20 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 20 ተተክቷል።

## 20. መቀጫን ስለማንሳት

1/ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያው መሠረት በታክስ ከፋዩ ላይ የተጣለው አስተዳደራዊ መቀጫ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ ለማድረግ ይችላል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የሚነሳው መቀጫ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 24 መሠረት የሚታሰበውን ወለድ አይጨምርም። »

መ/ በአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ /2/ ውስጥ «የሚፈለግበትን ተርን ኦቨር ታክስ__ካልከፈለ» ከሚለው ሐረግ ቀጥሎ ወይም «ይግባኝ ካላቀረበ» የሚል ሐረግ ተጨምሯል።

ሠ/ የአዋጁ አንቀጽ /30/ ንዑስ አንቀጽ /3/ ንዑስ አንቀጽ /4/ ሆኖ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /3/ ተጨምሯል።

3 / የባለሥልጣኑ ሠራተኛ ያለ በቂ ምክንያት አንድን ጉዳይ በማጓተት በግብር ከፋይ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በፍትሐብሄር ያለበት ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት በሚደረሰ እስራት ይቀጣል፡"

## 3. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግሥት ዝክረ- ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባሕር ዳር
ህዳር 12 ቀን 2004 ዓ.ም
አያሌዉ ጎበዜ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዚዳንት

C. Article of the proclamation is repealed and replaced by the following new article 20:

## 20. Waiver of penalty

1. Administrative penalties may be waived in accordance with directives issued by the tax Authority.
2. The administrative penalty to be waived in accordance with sub article (1) of this article may not include the interest computed in accordance with article 24 of this proclamation.

D. the Phrase “if fails to appeal” is added after the phrase “in default of paying the turn over tax” in sub-article 2 of article 21.

E. Sub- article 3 of article 30 of the proclamation is re-numbered as sub- article 4 and the following new sub- article 3 is added:

3/ the Authorities officer shall be held responsible for any damage caused to a tax payer by delaying, with out any good cause, the performance of his/her duty, such employee in addition to being held liable for the damages, shall, up on conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than one year and not more than two years.”

## 3. Effective Date

This proclamation shall enter in to force as of its publication in the Zikr- Hig Gazette of the Regional State.

Done at Bahir Dar
This 22th day of November,2011
Ayalew Gobezie
President of the Amhara National Region